# የኮሎምቢያ ግዛት መንግስት

የስራ ቅጥር አገልግሎቶች ዲፓርትመንት

MURIEL BOWSER
ከንቲባ

UNIQUE MORRIS-HUGHES
ጊዜያዊ ዳይሬክተር


## ለተከፋይ የቤተሰብ የስራ ፍቃድ ለኮሎምቢያ ግዛት አሰሪዎች እና ሰራተኞች ይፋ ማስታወቂያ

በአለምአቀፍ የተከፋይ የስራ ፍቃድ ማሻሻያ ህግ 2016 (“ተከፋይ የስራ ፍቃድ ህግ”) መሰረት፣ ሁሉም ሽፋን ያላቸው አሰሪዎች የእያንዳንዱ ሽፋን ያለው ሰራተኛቸው ደሞዝ መጠን 0.62% ያክሉን ለአለምአቀፍ ተከፋይ የስራ ፍቃድ አፈጻጸም ፈንድ ጁላይ 1፣ 2019 ላይ መዋጮ እንዲያደርጉ የሚጠየቁ መሆኑን በዚህ ማስታወቂያ መሰረት ተገልጿል። መዋጮዎች ከስራ ቅጥር አገልግሎቶች ዲፓርትመንት (DOES)፣ ከተከፋይ የቤተሰብ የስራ ፍቃድ ቢሮ (OPFL)፣ በገንዘብ መክፈያ ግብር ኤሌክትሮኒክ በሆነ መንገድ በየሩብ አመቱ ይሰበሰባል።

<u>ሽፋን ያለው ሰራተኛ</u>

ሽፋን ያለው ሰራተኛ ማለት ማንኛውም ሽፋን ያለው አሰሪ ሰራተኛ የሆነ እና ከ50% የሱን ወይም የሷን የስራ ጊዜ ለዚያ አሰሪ በኮሎምቢያ ግዛት ውስጥ በመስራት የሚያሳልፍ ማለት ነው፣ ወይም ሽፋን ካለው አሰሪ ጋር ያለው ቅጥር በግዛቱ መሰረት ያደረገ እና አብዛኛውን የሱን ወይም የሷን የስራ ጊዜ ለዚያ አሰሪ በኮሎምቢያ ግዛት ውስጥ በመስራት የሚያሳልፍ እና ከ50% የማይበልጥ የሱን ወይም የሷን የስራ ጊዜ ለዚያ ሽፋን ያለው አሰሪ በሌላ ግዛት በመስራት የሚያሳልፍ ማለት ነው።

<u>ሽፋን ያለው አሰሪ</u>

ሽፋን ያለው አሰሪ ማለት ማንኛውም ግለሰብ፣ ሽርክና፣ አጠቃላይ ተቋራጭ፣ ንኡስ ተቋራጭ፣ ማህበር፣ ኮርፖሬሽን ፣ የንግድ ማህበር፣ ወይም ማንኛውም የሰዎች ቡድን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ወይም በወኪል አማካኝነት ወይም ማንኛውም ሌላ ግለሰብ፣ በጊዜያዊ አገልግሎቶች ያሉ አገልግሎቶችን ወይም የሰራተኛ ኤጀንሲ ወይም ተመሳሳይ ተቋም፣ የሚቀጥር ወይም የሰራተኛን ደሞዝ፣ ሰዓት፣ ወይም የስራ ሁኔታዎችን የሚቆጣጠር እና ለሰራተኛው የስራአጥ መድን እንዲከፍል የሚጠየቅ ነው። በተጨማሪ ሽፋን ያለው አሰሪ በግል ተቀጣሪ ሆኖ በተከፋይ የስራ ፍቃድ ህግ መሰረት በተቋቋመው የተከፋይ-የስራ ፍቃድ ፕሮግራም ውስጥ ለመግባት የመረጠ ነው።

ሁሉም ሽፋን ካላቸው አሰሪዎች፣ ሽፋን ያላቸው ሰራተኞች፣ አመልካቾች፣ ብቁ ግለሰቦች፣ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች፣ የአቤቱታ መርማሪዎች፣ እና DOES OPFL ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶች በስልክ፣ ኢሜይል፣ እና በኦንላይን መንገድ በጁላይ 1፣ 2019 እና ከዚያ በኋላ ይደረጋል። የተከፋይ የቤተሰብ የስራ ፍቃድ አፈጻጸም(PFL) ፕሮግራም በተመለከተ ለበለጠ መረጃ፣ እባክዎ ይጎብኙ does.dc.gov።

በዚህ ማስታወቂያ ላይ አስተያየቶች እና የመረጃ ጥያቄ መላክ ያለበት ወደ፣


የስራ ቅጥር አገልግሎቶች ዲፓርትመንት
የተከፋይ የቤተሰብ የስራ ፍቃድ ቢሮ
4058 Minnesota Ave. NE
Washington, DC 20019
does.opfl@dc.gov